የWashington ግዛት ጠቅላይ አቃቤ ህግ ፅህፈት ቤት

# መብቶችዎን ይወቁ

## የስነ ተዋልዶ ጤና አጠባበቅ

## በWashington ግዛት ፅንስ ማስወረድ ህጋዊ እና የተጠበቀ ነው

### Washington ፅንስ ማስወረድ የማግኘት ዋስትና ይሰጣል:-

- በWashington ውስጥ ያለች ማንኛዋም ነፍሰ ጡር ሴት ፅንሱ ከማህፀን ውጪ ለመኖር ብቁ እስኪሆን ድረስ (በግምት ወደ 24 ሳምንታት እርግዝና) በማንኛውም ምክንያት ፅንስ የማስወረድ መሰረታዊ መብት አላት።[1]
- ፅንሱ ከማህፀን ውጪ ለመኖር ብቁ ከሆነ በኋላ፣ የነፍሰ ጡሯን ህይወት ወይም ጤና ለመጠበቅ ሲባል አስፈላጊ ከሆነ ፅንስ ማስወረድ በWashington ውስጥ ይፈቀዳል።[2]
- በWashington ውስጥ፣ በማንኛውም እድሜ ላይ ያሉ ሰዎች ለራሳቸው ውርጃ እንክብካቤ ፈቃድ የመስጠት መብት አላቸው። Washington ውስጥ ፅንስ ለማስወረድ ከአንድ ሰው ወላጅ፣ አሳዳጊ ወይም አጋር ፈቃድ አይጠየቅም።[3]

### በWashington የሚደረጉ ውርጃዎች ሚስጥራዊነታቸው የተጠበቀ ነው:-

- በWashington ውስጥ ያሉ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች በአጠቃላይ ስለ ነፍሰ ጡር ሰው ያለ የጽሁፍ ፍቃድ የጤና አጠባበቅ መረጃን ይፋ ማድረግ አይችሉም።[4]
- ከ2024 ጀምሮ፣ የWashington ንግዶች ያለ ሰው ፈቃድ የስነ ተዋልዶ እና የወሲብ ጤና መረጃን ጨምሮ የተወሰኑ የጤና መረጃዎችን ይፋ ማድረግ ወይም መሸጥ አይችሉም።[5]
- ነፍሰ ጡር ሴቶች ፅንስ ማስወረድን የሚመለከቱ መረጃዎች በሙሉ ለጤና መድን ዋስትናቸው ለሚከፍለው ሰው (ወላጆችን ጨምሮ) ሳይሆን ለራሳቸው እንዲላክ የማድረግ ህጋዊ መብት አላቸው።[6]
- ይህ መረጃ የት እንደሚላክ ለመቀየር 'Confidentiality Request Form (የምስጢራዊነት መጠየቂያ ቅፅን)' ያትሙ፣ ይሙሉ፣ ይፈርሙ እና ለጤና መድን ኩባንያዎ ይላኩ።[7] ይህንን ሚስጥራዊነት ለመጠየቅ ወደ ጤና መድን ኩባንያዎ መደወልም ይችላሉ።

### የWashington የውርጃ አገልግሎቶች መድን ሽፋን ያስፈልገዋል:-

- እርግዝና ወይም የወሊድ አገልግሎትን የሚሸፍኑ ሁሉም በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉ የጤና ዕቅዶች ፅንስ ማስወረድ አገልግሎቶችን ጨምሮ የህክምና/መድሀኒት ፅንስ ማስወረድ (ክኒኖች እርግዝናን ለማቆም ጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ) ለመሸፈን በህጋዊ መንገድ ይጠየቃሉ።[8] በአጠቃላይ፣ የጤና ዕቅዶች ለውርጃ እንክብካቤ የወጪ መጋራት ላይሆኑ ይችላሉ።[9]
- የWashington የጤና መድን ፕሮግራም አፕል ሄልዝ (ሜዲኬይድ) Apple Health (Medicaid) ብቁ ለሆኑ ታካሚዎች የፅንስ ማስወረጃ እንክብካቤን ይሸፍናል።[10]
- መድን ከሌለዎት፣ ለውርጃ ለመክፈል ሊረዱዎት የሚችሉ የክልል ፕሮግራሞች አሉ።[11]

### ከሌሎች ግዛቶች የመጡ ነፍሰ ጡር ሰዎች በWashington የውርጃ እንክብካቤ ሊያገኙ ይችላሉ:

- ከሌሎች ግዛቶች ነፍሰ ጡር ሰዎች ለውርጃ አገልግሎት ወደ Washington መምጣት ይችላሉ።[12]
- የWashington ህግ አስከባሪዎች፣ ኤጀንሲዎች እና ፍርድ ቤቶች ከስቴት ውጭ ከሚደረጉ የሲቪል እና የወንጀል ምርመራዎች ወይም በWashington ውስጥ ከሚቀርቡት እንክብካቤ ጋር የተያያዙ የህግ እርምጃዎች ጋር እንዳይተባበሩ የተከለከሉ ናቸው።[13]
- ከ2024 ጀምሮ፣ በWashington ውስጥ የተሰበሰቡ አንዳንድ የጤና መረጃዎች፣ ከግዛት ውጪ ወደ Washington ከሚገቡ ነዋሪዎች ጨምሮ፣ ያለፍቃድ ሊሰበሰቡ፣ ሊጋሩ ወይም ሊሸጡ አይችሉም።[14]
- ፈቃድ ያላቸው አገልግሎት ሰጪዎች በWashington ህጋዊ የውርጃ እንክብካቤን ስለሚሰጡ ተግሣጽ አይደረግባቸውም፣ ሌላ ግዛት የዲሲፕሊን እርምጃ ቢወስድም እንኳ።[15]

---

1 RCW (Revised code of Washington, የWashington የተከለሰ ኮድ) 9.02.100, .110, .170።
2 RCW 9.02.110።
3 RCW 9.02.100; *ተጨማሪ ለማየት* የ2022 ህጎች፣ ምዕ. 65፣ § 1(5)።
4 RCW 70.02.020 (1);; 45 CFR (Code of Federal Regulations, የፌዴራል ደንቦች ኮድ) § 164.502።
5 የ2023 ህጎች፣ ምዕ. 191 (Washington የእኔ ጤና የእኔ መረጃ ህግ)። ንግዶች ከማርች 31፣ 2024 ጀምሮ ማክበር አለባቸው፣ እና ትናንሽ ንግዶች ከጁን 30፣ 2024 ጀምሮ ማክበር አለባቸው።
6 WAC (Washington Administrative Code, የWashington ማስተዳደሪያ ኮድ) 284-04-510።
7 ይህ የጥያቄ ቅጽ የሚገኘዉ በሚከተለው ላይ ነው:- https://www.insurance.wa.gov/sites/default/files/documents/confidentiality-request-form_0.pdf።
8 RCW 48.43.073:- https://www.insurance.wa.gov/coverage-abortion-services።
9 የ2023 ህጎች፣ ምዕ. 194 (RCW 48.43.073 ማሻሻል)። HSA (Health Savings Account, የጤና የቁጠባ መለያ) ብቁ የሆነ የጤና እቅድ ካልዎት፣ እቅድዎ ለውርጃ እንክብካቤ የወጪ መጋራትን ሊመሰርት ይችላል፣ ነገር ግን ከቀረጥ ነፃ የሆነ መዋጮ እና ከHSA የሚወጡትን የመጠየቅ ችሎታዎን ለመጠበቅ በሚያስፈልግ ዝቅተኛ ደረጃ ብቻ።
10 Apple Health (https://www.hca.wa.gov) ፅንስ የማስወረድ አገልግሎቶችን፣ ፅንስ ከማስወረድ በኋላ እንክብካቤን እና ከፅንስ ማስወረድ በኋላ የቤተሰብ ምጣኔን ይሸፍናል። የጤና መድን ከሌልዎት እና ለApple Health ብቁ ካልሆኑ፣ ከጤና እንክብካቤ ክሊኒክ፣ ከውርጃ አገልግሎት አቅራቢ ወይም ከሰሜን ምዕራብ ውርጃ የመዳረሻ ፈንድ (https://nwaafund.org/) እርዳታ ማግኘት ይችሉ ይሆናል።
11 ብቁ መሆንዎን ለማወቅ፣ ይህንን የቅድመ ማጣሪያ ቅጽ መጠቀም ይችላሉ:- https://www.washingtonconnection.org/prescreening/home.go?action=Introduction።
12 RCW 9.02.110።
13 የ2023 ህጎች ፣ምዕ.193 *ተጨማሪ ለማየት፣* RCW 9.02.100።
14 የ2023 ህጎች፣ ምዕ. 191።
15 የ2023 ህጎች፣ ምዕ. 192። አገልግሎት ሰጪዎች ፅንስ ማስወረድ እንክብካቤን የመስጠት ወይም የመደገፍ ህጋዊ መብቶቻቸውን በሚመለከት ጥያቄ ካላቸው፣ ወይም በቁጥጥር ስር ሊውሉ ወይም ሊከሰሱ ዛቻ ከደረሰባቸው፣ ያለ ክፍያ (በነጻ) የህግ ምክር እና ውክልና https://abortiondefensenetwork.org/ በኩል ይገኛል።

### Washington ውርጃን እና የወሊድ መከላከያን በደህና የማግኘት መብትዎን ይጠብቃል፡-

- የWashington ህግ ማንኛውም ሰው የፅንስ ማስወረድ እንክብካቤን ጨምሮ ወደ የጤና እንክብካቤ መስጫ ተቋማትን እንዳይሄዱ ጣልቃ መግባት ወይም መከልከልን ይከለክላል፡፡[16]
- ከሐኪሞች እንዲሁም ከሐኪም ረዳቶች እና ከፍተኛ የተመዘገቡ ነርስ ሐኪሞች የፅንስ ማስወረድ እንክብካቤን ማግኘት ይችላሉ፡፡[17]
- ከህክምና አቅራቢ ጋር በስልክ ወይም በኮምፒውተር (የቴሌሄልዝ ቀጠሮ) መገናኘት እና የውርጃ ክኒኖችን በWashington ግዛት ውስጥ ወደሚገኝ አድራሻ በፖስታ እንዲላክልዎት ማድረግ ይችላሉ፡፡[18]
- ሆስፒታል ወይም ሌላ ቀጣሪ የጤና እንክብካቤ አቅራቢው በታካሚው ህይወት ላይ አደጋ የሚፈጥሩ ውስብስብ የእርግዝና ሁኔታዎች (የፅንስ መጨንገፍ እና ከማህፀን ውጪ እርግዝናን ጨምሮ)፣ የማይስተካከሉ ውስብስብ ሁኔታዎች ወይም በታካሚው የሰውነት ተግባራት ላይ እክል በሚፈጥሩ ጉዳዮች ላይ ህመምተኛውን ከማከም ሊያግዱ አይችሉም፡፡[19]
- በWashington ግዛት ውስጥ በማንኛውም እድሜ የወሊድ መከላከያ የማግኘት መብት አልዎት፡፡[20]

### "የቀውስ እርግዝና ማዕከላት" ይወቁ፡-

- የስነ ተዋልዶ ጤና አጠባበቅ አገልግሎት እንሰጣለን የሚሉ ነገር ግን ፅንስ ለማስወረድ ወይም ፅንስ ወደሚያስወርዱ አገልግሎት አቅራቢዎች ሪፈር ለማድረግ እምቢ የሚሉ ክሊኒኮችን ይጠንቀቁ፡፡ ይህ ዓይነቱ ክሊኒክ በተለምዶ "የቀውስ የእርግዝና ማዕከል" ተብሎ ይጠራል፡፡
- "የቀውስ የእርግዝና ማዕከላት" የታካሚ እንክብካቤን በሰራተኞች ወይም ፈቃድ በሌላቸው የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች እና ያልተሟላ የህክምና ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ክሊኒኮች ለHIPPA (Health Insurance Portability and Accountability Act, የጤና መድን ተንቀሳቃሽነት እና ተጠያቂነት ህግ) ተገዢ አይደሉም እና የጤና መረጃዎን በሚስጥር ላይዙ ይችላሉ፡፡[21]

### የፅንስ ማስወረድ እንክብካቤ ሰጪዎችን ማግኘት፡-

- የሰሜን ምዕራብ የውርጃ መዳረሻ ፈንድ እና ብሔራዊ የውርጃ ፌዴሬሽን በWashington ውስጥ ያሉ የውርጃ አገልግሎት ሰጪዎችን ዝርዝር ይይዛሉ፡፡[22]
- በApple Health ለሚተዳደር እንክብካቤ እቅድ ወይም Apple Health ለነፍሰ ጡር ሴቶች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሁለቱም የውርጃ አገልግሎቶችን፣ የድህረ ውርጃ እንክብካቤን እና የድህረ ውርጃ የቤተሰብ ምጣኔን ይሸፍናሉ፡፡
- ከWashington የመጣ Providence Health Plan ሽፋን ካልዎት፣ ከDOH (Department of Health, የጤና መምሪያ) ክፍያ ለመቀበል ከተስማማ አቅራቢ አገልግሎት እስከተቀበሉ ድረስ DOH ለውርጃ አገልግሎቶችዎ ይከፍሉልዎታል፡፡[23]

### የWashington ህግ ለወሊድ ቁጥጥር እና ለድንገተኛ ጊዜ የእርግዝና መከላከያ ልዩ ጥበቃዎች አሉት፡-

- የሕክምና ምክንያት (እንደ አለርጂ) ከሌለ ወይም ፋርማሲው መድሃኒቱ ከሌለው እና በፍጥነት ማግኘት ካልቻለ በስተቀር የWashington ፋርማሲዎች በመድኃኒት ፅንስ የማስወረድ፣ ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ እና የወሊድ መቆጣጠሪያ ማዘዣዎችን ጨምሮ ሁሉንም ትክክለኛ የሆኑ የሐኪም ማዘዣዎችን መሙላት አለባቸው፡፡[24]
- የWashington ሕግ በአጠቃላይ ሁሉም በግዛት የሚተዳደሩ የጤና ዕቅዶች (የተማሪ ጤና ዕቅዶችን ጨምሮ) የአደጋ ጊዜ የወሊድ መከላከያ እና የሐኪም ማዘዣ የማያስፈልጋቸው ዘዴዎችን ጨምሮ፣ እያንዳንዱን በFDA (Food and Drug Administration, የምግብ እና መድሐኒት አስተዳደር)
- ተቀባይነት ያለው የወሊድ መከላከያ ዘዴ ያለ ምንም ወጪ እና ያለ ገደብ ወይም መዘግየቶች እንዲሸፍኑ ይጠይቃል፡፡[25]
- ሁሉም የድንገተኛ ክፍል ያላቸው ሆስፒታሎች ለወሲብ ጥቃት እንደ ህክምና አማራጭ ድንገተኛ የወሊድ መከላከያ ማቅረብ አለባቸው፡፡[26]

---

16 RCW 9A.50.020፡፡
17 RCW 9.02.110፡፡
18 እቅድ ሐ ይህንን የቴሌሄልዝ አገልግሎት አቅራቢዎች ዝርዝር ያቀርባል፣ https://www.plancpills.org/states/washington፡፡ ክሊኒኮች የሚያካትቱ Cedar Rivers Clinics እና Planned Parenthood፡፡
19 RCW 70.400.020፡፡
20 RCW 9.02.100፡፡
21 የፌደራል ጤና ጥበቃ ጥበቃዎች (HIPAA በመባል የሚታወቁት) በአጠቃላይ ፈቃድ ላላቸው የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች እና ሰራተኞቻቸው እና ወኪሎቻቸው ብቻ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡ 45 CFR § 164.502፡፡ አዲሱ የWashington የጤና መረጃ የግላዊነት ህግ በ2024 ተግባራዊ ይሆናል፡፡ የ2023 ህጎች፣ ምዕ. 191፡፡
22 እነዚህ መርጃዎች በWashington የጤና መምሪያ ድረ-ገጽ፣ https://doh.wa.gov/you-and-your-family/sexual-and-reproductive-health/abortion ላይ ተዘርዝረዋል፡፡ *ተጨማሪ ይመልከቱ* የሰሜን ምዕራብ የውርጃ መዳረሻ ፈንድ (www.abortionfinder.org)፤ የብሔራዊ ውርጃ ፌዴሬሽን (The National Abortion Federation) (www.prochoice.org/patients/find-a-provider)፡፡
23 https://doh.wa.gov/you-and-your-family/sexual-and-reproductive-health/abortion/increasing-access-reproductive-choice፡፡
24 WAC 246-945-415; *Stormans, Inc. v. Wiesman*, 794 F.3d 1064 (9th Cir. 2015)፡፡
25 RCW 48.43.072; WAC 284-43-5150; https://www.insurance.wa.gov/reproductive-and-birth-control-health-rights፡፡
26 RCW 70.41.350; WAC 246-320-286፡፡